በውጪ አገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ወደ አገር ቤት የሚልኩልን የውጪ ምንዛሪ ለአገራችን ኢኮኖሚ እድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረክታል፡፡ የቅርብ ጊዜ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፣ በዚህ መንገድ የምናገኘው የውጭ ምንዛሪ ከወጪ ንግዳችን ከሚገኘው ገቢ የበለጠ ነው፡፡

ይሁን እንጂ በውጭ ምንዛሪ ግኝት ላይ በርካታ ተግዳሮቶች ይስተዋላሉ፡፡ ለዚህም በርካታ ምክንያቶች ያሉ ሲሆን፣ ዋና ዋናዎቹ:-

- ምንዛሪው በትንሹ 10 በመቶ የአገልግሎት ክፍያ በሚጠይቁ ውስን ገንዘብ አስተላላፊ ድርጅቶች በኩል ወደ አገር ቤት መላኩ፤ እና
- የጥቁር ገበያ እና ሌሎች ከባንክ ውጪ ያሉ የውጪ ምንዛሪ ማግኛ ዘዴዎች መስፋፋታቸው ናቸው፡፡

ወቅቱን ያገናዘበ እና በቴክኖሎጂ የታገዘ የገንዘብ መላኪያ መተግበሪያ መጠቀም የተግዳሮቶቹ መፍትሔ ዋነኛ አካል በመሆኑ፣ ባንካችን በኢትዮጵያ ፈር ቀዳጅ የሆነ ዲጂታል የውጭ ምንዛሪ መላኪያ ፕላትፎርም በተግባር ላይ አውሏል። የዚህ ፕላትፎርም ኦፊሴላዊ መለያ ኢትዮዳይሬክት (EthioDirect) ሲሆን፣ ፕላትፎርሙ የተበለጸገው በባንካችን እና በኢግል ላይን ሲስተም ቴክኖሎጂ ኃ/የተ/የግ/ኩባንያ ትብብር ነው።

ኢትዮዳይሬክት ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ፣ ደኅንነቱ አስተማማኝ እንዲሁም የሞባይል እና የዌብ መተግበሪያዎችን ያካተተ ፕላትፎርም ነው። ፕላትፎርሙ ምንም ዓይነት የአገልግሎት ክፍያ የማይጠየቅበት መሆኑ ደግሞ የተለየ ያደርገዋል፡፡ ሌላው በጎ ጎኑ በመተግበሪያው አማካይነት የውጭ ምንዛሪን መላክ እጅግ ቀላል መሆኑ ነው።

ኢትዮዳይሬክት፡-

- እንደ ቪዛ እና ማስተርካርድ ያሉ ዓለም አቀፍ የክፍያ ካርዶችን በመጠቀም ገንዘብ መላክ ያስችላል፤
- የአንድሮይድም (Android) ሆነ የአይ.ኦ.ኤሰ (IOS) ኦፕሬቲንግ ሲስተም በሚጠቀሙ ስልኮች ላይ በሙሉ ይሠራል፤
- ከ5 እስከ 1,000 ዶላር ድረስ የገንዘብ መጠን ይላክበታል፤

- በመተግበሪያው አማካይነት ለመጀመሪያ ጊዜ ገንዘብ ለተቀበለ ደንበኛ የተላከለትን የገንዘብ መጠን 10 በመቶ በጭማሪ ጉርሻነት ያስገኛል፤
- ደንበኞች መተግበሪያውን ከፕሌይ ስቶር(Play Store ወይም ከአፕ ስቶር (App Store) በነጻ ወደ ሞባይል ስልካቸው በማውረድ ሊጠቀሙት ይችላሉ፤
- በቅርብ ግዜ ውስጥ ደግሞ ወደ https://www.ethiodirect.com ድረ ገጽ በመግባት በቀጥታ ገንዘብ መላክ የሚችሉበትን አማራጭ ያቀርባል።

በዚህ ወቅት የውጭ ምንዛሪ በኢትዮዳይሬክት በኩል ወደ ተቀባዩ የሚደርሰው ወደ ባንክ ሒሳቡ ሲላክ ነው። በቀጣይ ግን ላኪው ገንዘቡን ወደ ተቀባዩ የሲቢኢ ብር ዋሌት ማስገባት ወይም ተቀባዩ ጥሬ ገንዘቡን ከባንካችን ቅርንጫፍ መውሰድ የሚችልበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡

በኢትዮዳይሬክት አማካይነት ወደ ኢትዮጵያ በቀጥታ ገንዘብ መላክ የሚቻለው ለጊዜው ከሚከተሉት አገራት ነው፡-

| | | |
|---|---|---|
| 1. ካናዳ | 4. ጣልያን | 7. የተባበሩት አረብ ኤሚሬቶች |
| 2. እሥራኤል | 5. ደቡብ አፍሪካ | 8. እንግሊዝ |
| 3. አሜሪካ | 6. ስዊድን | 9. ሳኡዲ ዐረቢያ፡፡ |

በቀጣይ ደግሞ ባንካችን ከቪዛ ኢንተርናሽናል ጋር በሚያደርገው ስምምነት መሠረት ከሌሎች አገራትም መላክ የሚቻልበትን አማራጭ ያሰፋል፤ ይኸውም በየጊዜው ለደንበኞች የሚገለጽ ይሆናል፡፡

በአጠቃላይ ሲታይ ኢትዮዳይሬክት፡-

- የባንካችንን የውጪ ምንዛሪ ሐዋላ አገልግሎት አሰጣጥ በከፍተኛ ደረጃ አዘምኖ ያቀላጥፋል፤
- የውጪ አገር ሐዋላ መላክና መቀበልን በቀላሉና ያለምንም ክፍያ ለማከናወን ያስችላል፤
- ደንበኞች ጥቁር ገበያን ትተው በሕጋዊ መንገድ ገንዘብ እንዲልኩ ያበረታታል፤
- ለአገራችን የልማት ክንውኖች በቂ የውጪ ምንዛሪ አቅርቦት እንዲኖር ትልቅ አስተዋፅኦ ያበረክታል፡፡

ስለሆነም፣ ባንካችን በውጪ አገራት የሚገኙ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በሙሉ ኢትዮዳይሬክትን በመጠቀም በዓለም አቀፍ የክፍያ ካርዶች ገንዘብ መላክ እና መቀበል እንዲጀምሩ በታላቅ አክብሮት ይጋብዛል፡፡ በተጨማሪም በአገር ውስጥ የሚገኙ የውጭ ምንዛሪ ተቀባዮች አገልግሎቱን በውጭ አገር ለሚኖሩ ዘመድ ወዳጆቻቸው እንዲያስተዋውቁ በአክብሮት ይጠይቃል፡፡

ለበለጠ መረጃ ወደ 951 በነጻ ይደውሉ፡፡